# የግላዊነት መመሪያ

በዚህ የግላዊነት መመሪያ (“መመሪያ”)፣ እኛ፣ ኳልኮም ጠቅላላ እና የእኛን ተያያዥ ቅርንጫፎች (በጠቅላላ “እኛ” “እኛ” “የእኛ”)፣ መረጃን እንዴት እንደምንሰበስብ፣ እንደምንጠቀም፣ እንደምንሰራ እና እንደምናስተላልፍ እንገልጻለን፡፡ ኳልኮም ጠቅላላ እና የእኛን ተያያዥ ቅርንጫፎች ስር የምናስተዳድረውን መረጃ በንግድ (ህጋዊ አካላት)፣ የንግድ ስራ ሂደቶች እና የመረጃ ስርአቶች የምናጋራ ዓለም አቀፍ ድርጅት ነን፡፡

ስለዚህ፣ ለዚህ መመሪያ፣ በእኛ ላይ ተፈጻሚነት በርካታ የግላዊነት እና የመረጃ ጥበቃ ህጎችን ለመሸፈን “የግል መረጃ” የሚለውን ቃል እንጠቀማለን “የግል መረጃ” ማለት ማንነቱ ከተለየ ሰው ጋር ተያያዥነት ያለው ወይም ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ተፈጥሮአዊ ሰውን ለመግለጽ በራሱ ወይም ከሌሎች መረጃዎች ጋር በማጣመር የምንጠቀምበት ቃል ነው፡፡

## ወሰን

ይህ መመሪያ በድህረገጾቻችን፣ በምርቶቻችን፣ በአገልግሎቶቻችን፣ በሶፍትዌሮቻችን፣ ወይም ከዚህ መመሪያ ጋር ቀጥታ አገናኝ የምንለቅባቸው አፕልኬሽኖቻችን (በአጠቃላይ "አገልግሎቶቻችን") ሁሉ ላይ ይተገበራል፡፡ ይህ መመሪያ በአገልግሎቶቻችን ከሚሰብሰቡ መረጃዎች ውጪ ሌላ የራሳቸው የሆነ የግላዊነት መመሪያ ያላቸውን መረጃ ሰብሳቢ እና ተጠቃሚዎችን አይሸፍንም፡፡ አንዳንዴ፣ ከምርምሮችና ልዩ ልዩ ከሆኑ ደህረገጾች ጋር በተያያዘ ይህንን መመሪያ እንመለከታለን፤ ለምሳሌ፣ የእኛ የስራ ድህረ-ገጾች በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ይህ መመሪያ የሚከበረው በተጠቀሰው ልዩ ማስታወቂያ ወይም ፍቃድ ጥያቄ ውስጥ እንደተሻሻለው ነው (ለምሳሌ፡- እንደተሰበሰበው መረጃ ወይም እንደተሰበበት ምክንያት)፡፡

## የመረጃ አይነቶች እና የአሰባሰብ ዜዴዎች

ከታች በተሰበሰቡት መንገዶች አማካኝነት የተለያዩ ዓይነት የግል መረጃዎችን እንሰበስባለን፡፡ እርስዎ በምንሰበሰባቸው መረጃዎች ላይ ምርጫ አለዎት፡፡ መረጃ እንዲያቀርቡ በሚጠየቁበት ጊዜ አለመላክ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን መረጃውን ካልሰጡን እኛ ምንስጣቸውን ምርቶች እና አገልግሎቶች የመጠቀም አቅምዎ ይቀንሳል ወይም ይገደባል፡፡

**የሚያስገቡት መረጃ፡፡** ስምዎን፣ የኢሜይል አድራሻ(ዎች)፣ የሜይል አድራሻ(ዎች)፣ ስልክ ቁጥርዎን፣ ከእኛ መረጃ ሲጠይቁ በሚወክሉት ንግድ ላይ የተዛመዱ መረጃዎች ፤ ይመዝገቡ፣ ምርት ወይም አገልግሎት ይጠይቁን ይዘዙን አሊያም ይህን መረጃ ይላኩልን፡፡ ከሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የክፍያ መረጃ (ለምሳሌ፡- ክሬዲት ካርድ ቁጥር እና ተያያዥነት ያላቸው ገላጭ መረጃዎችን) የስልክ ቁጥር እና የክፍያ መጠየቂያ እና የማጓጓዣ አድራሻዎችን እንሰበስባለን፡፡

**በቀጥታ ከድህረ-ገጻችን የምንሰበስባቸው መረጃዎች** ድህረ-ገጻችን አንዱን በሚጎበኙበት ጊዜ፣ ጠቅላላ መረጃዎች ከኮምፒውተርዎ ወይም ከሞባይልዎ የሚጠቀሙበትን ብሮዘር ዓይነት፣ ኦፕሬቲንግ ሲስተም፣ አይ.ፒ. አድራሻ እና እየተጠቀሙበት ያሉት በስልክዎ ከሆነ የስልክዎን ዓይነት ምን እንደሆነ መረጃ ይሰበሰባል፡፡ በተጨማሪም፣ ድህረ ገጻችንን እንዴት እንደሚጠቀሙ መረጃ እንሰበስባለን፣ ማለትም የጎበኙበትን ቀን እና ጊዜ፣ የጎበኙትን ገፅ ምን ያህል እንደሆነ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደቆዩ፣ ለስንት ጊዜ ወደዚህ ድህረ ገፅ እየተመለሱ እንደጎበኙ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች እንሰበስባን፡፡

**ኩኪዎች**፡፡ ስለ ድህረ-ገጻችን አጠቃቀምዎ ኩከኖዎች፣ ቢኮኖች ወይም ተመሳሳይ ቴክኖሎጂዎችን እንጠቀማለን ፡፡ ኩኪ የምንለው ድህረገጹን በሚጠቀሙበት ጊዜ በኮምፒተሮ ሀርድ ድራይቭ ውስጥ የሚቀመጥ የጹሑፍ ፋይል ነው፡፡ ጣቢያዎቻችንን እና አገልግሎቶቻችንን ለማስኬድ ኩኪዎችን እንጠቀማለን፡፡ ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡- (1) ወደ ድህረ-ገጹ ሲመለሱ ደግመው ተመሳሳይ መረጃን እንዳያስገቡ እንድናስታውሶት (2) በድህረ-ገጹ ላይ ብዙ ይዘት ወይም አቅርቦት ይሰጦታል፡፡ (3) የድህረ-ገጹን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ምርምር ለማድረግ ይዘት አገልግሎቶቻችንን ለማሻሻል ድምር እስታቲስቲኮችን ለመፍጠር (4) የድረ-ገጾቻችንን እና የአገልግሎታችንን ደህንነት ለመጠበቅ፡፡

በድህረ-ገጹ ላይ ሌሎች ድርጅቶች የድህረ-ገጽ ትንተና አጋሮች አስተዋዋቂዎች ወይም የማስታወቂያ ኔትወርኮች ኩኪዎቻቸውን ወይም ዌብ ቢኮኖቻቸውን እንዲያዘጋጁ ወይም እንዲጠቀሙ እንፈቅዳለን፡፡

ለምሳሌ፡- ሶስተኛ ወገን ኩባንያዎችን ስለ እኛ ማስታወቂያዎችን እንዲያስተዋውቁ ወይም የሌሎች ኩባንያዎችን ማስታወቂያ በድረ-ገጻችን ላይ ለማሳየት እንጠቀማለን ፡፡

እንዚህ ሶስተኛ ወገን ኩባንያዎች እኛን ጨምሮ የሌሎች ደንበኞቻቸውን የማስታወቂያ ውጤታማነት ለመጠበቅ ኩኪዎችንና ዌብ ቢኮኖችን ይጠቀማሉ ፡፡ ይህን ለማድረግ፣ እነዚህ ኩባንያዎች የኛንና ሌሎች ድህረ-ገጾችን የሚጎበኙበትን መረጃ ይጠቀማሉ፡፡ ማስታወቂያ የታየበትን ቀን ወይም ጊዜ ኩኪ ውስጥ የሚገኝ ልዩ ማሳወቂያ እና የሚጠቀሙበት መሳሪያ አይ.ፒ. አድራሻን ያጠቃልላል፡፡ እርስዎ የፈለጉትን ዓይነት ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን ማየት ከፈለጉ በራስዎ ፍላጎት አድርገው ማስተካከል ይችላሉ፡፡ በእርስዎ ፍላጎት ተስማሚ አድርገው ለማስተካከል ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ይህን ጽሑፍ ይመልከቱ ይህ የምርጫውን መርጦ መውጣት.

ኩኪዎችን አለመጠቀም ይችላሉ፣ ግን ይህን በማድረግዎ ጥቂት ባህሪያትን ለመጠቀምና ሙሉ አቅርቦቶቻችንን ለመጠቀም አይችሉም፡፡ የኩኪ ምርጫዎትን እንዴት መቀየር እንደሚችሉ ለመማር "Help" የሚለውን ይጫኑ፡፡ ለበለጠ መረጃ እባክዎ ኩኪ ፖሊሲ ይመልከቱ ፡፡

**ሶፍትዌር እና አፕልኬሽኖች፡-** Qualcomm Incorporated's subsidiaries የተለያዩ የስልክዎን አገልግሎት ባትሪዎን ለመቆጠብ ደህንነቱን ለመጠበቅ ሌሎችንም ጥቅሞችን የሚሰጡ ሶፍትዌሮችንና አፕልኬሽኖችን ይሰራሉ፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ያካባቢ መረጃ ልዩ መለያዎች (chipset serial number or international subscriber ID ) በመሳሪያዎች ላይ የተጫኑና በስራ ላይ የሚገኙ አፕልኬሽኖችን የተዋቀረበትን መረጃ አሰራሩ ሞዴል ገመድ አልባ አገልግሎቱን የተሰራበት ሶፍትዌር መረጃ እና የመሳሪያውን የአሰራር ሁኔታ Chipset አሰራር የባትሪ አጠቃቀም እና የሙቀት መረጃዎችን እንሰበስባለን፡፡ ተጨማሪ ይወቁ

**የሶስተኛ ወገን ምንጮች፡-** በመረጃ ደላላዎች ከማህበራዊ ኔትወርኮች ከሌሎች አጋሮች ወይም ህዝባዊ ምንጮች መረጃዎችን እናገኛለን፡፡

## የስብስብ ዓላማ፤ የመረጃ አጠቃቀም፡፡

የግል መረጃዎን በእርስዎ ፈቃድ እና/ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ምርቶቹን ለማቅረብ፣ ንግድ ለማስፈም፣ ውሎችን እና ህጋዊ ግዴታችንን ለመወጣት፣ የስርዓቶቻችንንና ደንበኞቻችንን ደህንነት እና ሌሎች ሕጋዊ ፍላጎቶችን መፈጸም፡፡ መረጃን የምንሰበስብበት እና የምንጠቀምበት አላማዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

- ለላኩልን ጥያቄ መልስ እንድንሰጥዎ ለምሳሌ፤ የመረጃ ጥያቄዎችን ወይም አገልግሎት ለማግኘት የሚልኩትን ጥያቄ አሊያም የምርት ግዢ ጥያቄዎትን፤
- የጠየቁትን፤ አገልግሎት ለማቅረብ፣ ለማደራጀት እና ደህንነቱን ለመጠበቅ
- አገልግሎታችንን እና ስርዓታችንን ለማስተዳደር፣ ለመጠበቅ፣ እና ለማሻሻል፣ አዲስ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ለመገንባት፣ እና ለሌሎች የውስጥ የንግድ አላማዎች፤
- የአገልግሎታችን ተጠቃሚዎችን በተሻለ ለማወቅ ስለአገልግሎታችን ስታተስቲክስ ለመስራት እና በእኛ ድህረ-ገጽ እና አገልግሎት የሚኖሮዎትን ቆይታ በእርስዎ ፍላጎት፡ ተስማሚ ለማድረግ፤
- ስለ ቴክኖሎጂዎቻችን ምርቶቻችን እና አገልግሎቶቻችን መረጃ ለእርስዎ ለማድረስ የምርት ወይም የአገልግሎት ልቀቶች፣ ዜና እና ሌሎች ግንኙነቶች፤ እናም
- ማንኛውም ሌላ ጥቅም በዚህ መመሪያ ውስጥ ወይም መረጃ በምንሰበስብበት ጊዜ እናብራራለን፡፡

አላማዎቹን ለማሳካት፣ እና በሚተገበረው ህግ እስከሚፈቀደው ድረስ፣ ከተለያዩ ምንጮች የምንሰበስባቸውን የተለያዩ የመረጃ ዓይነቶች እናጣምራለን፡፡

## መረጃን የምናስቀምጥበትና የምናስኬድበት ቦታ፡፡

በ United States እና በአለም ዙሪያ በሰርቨሮች ላይ ስናስቀምጥ፤ ያለ ገደብ በኢሲያና የአውሮፓ ኢኮኖሚ አካባቢንም ያጠቃልላል፡፡ ሁሌም የግል መረጃን ስናስቀምጥ ወይም ስናስኬድ በመመሪያችን፤ መሰረት መሆኑን ከመመሪያው አንጻር እና፤ ከሚተገበረው፤ ህግ፤ ጋር፤ እንደማይጋጭ፤ እናረጋግጣለን፡፡

የግል መረጃን፤ ከአውሮፓዊያን የኢኮኖሚ አካባቢ ወደ ሌላ አገሮች፤ እናስተላልፋለን፣ አንዳንዶቹ አገሮች በአውሮፓ ኮሚሽን በቂ የመረጃ ጥበቃ እንደሌላቸው ይታሰባል፡፡ ይህን ስናደርግ የማስተላለፍ ሁኔታውን ተፈጻሚ ለማድረግ የተለያዩ ህጋዊ ስልቶችን እንጠቀማለን ( የእርስዎን ስምምነት ወይም ህጋዊ ውል) ፡፡

## የግል መረጃዎችን ይፋ ማድረግ፡፡

በኩባንያዎ ውስጥ (የግል ቅርንጫፎቹን ጨምሮ) የግል መረጃዎን እንሰበስባለን፣ እና በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ለተቀመጡት ዓላማዎች በእኛ ምትክ ስለ እኛ ውስጥ መረጃን ለሚሰሩ ለሶስተኛ ወገን አቅራቢ ወይም አገልግሎት ሰጪዎች መረጃን እንጋራለን፡፡ እንዲሁም ለንግድ አጋሮቻችን ተቀጣሪዎችና ሰራተኞች ስልጠናዎች እና ሌሎች አገልግሎቶችን እንሰጣለን፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ከስልጠናችን እና ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ከተመለመሉ የንግድ ደንበኞች ጋር መረጃን እንጋራለን፡፡ እንደዚሁም በህግ ወይም በተሰጠን መሰረት የእኛን ወይም የሌሎችን ህጋዊ መብቶችን ለመጠበቅ ወይም ለመተግበር በሚያስፈልግ መልኩ ውሂብዎን ልንጋራ እንችላለን ለምሳሌ, ከህግ አስከባሪ ባለስልጣናት ጥያቄዎች እና ከፍርድ ቤት ሂደቶች ጋር በተገናኘ መልኩ ያለገደብ፡፡ ከተጣራ ወይም ከእውነተኛ እሴት ጋር ውሕደት፣ ሽግግር ወይም የሁሉም ወይም የእኛ ንግዳዊ አካል በሆኑ ሌሎች ድርጅቶች ላይ መረጃዎን ልንጋራ ወይም ልናስተላልፍ እንችላለን፡፡ በመጨረሻም ፍቃድዎን በሰጡን ቦታ ላይ የግል መረጃዎትን እናካፍላለን፡፡

## ምርጫዎ

***መርጦ-መግቢያ/መውጫ*** በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፣ እንደ የመረጃ መሰብሰብ መጠቀም ወይም ማጋራቶች መረጠው መውጣት ይችላሉ፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ምርጫዎን እናከብራለን፡፡

**Access**። እንደምናስቀምጠው የእርስዎን የግል መረጃ ለመዳረስ ከፈለጉ, ወይም ያስገቡት የግል መረጃ ከእንግዲህ ትክክል፣ የአሁን ወይም የተሟላ ካልሆነ፣ እናም ለማዘመን ከፈለጉ፣ [https://www.qualcomm.com/site/access-request/contact] ስለእርስዎ ሊኖረን የምንችለውን የግል መረጃ እንድንለይ እንዲያግዘን እባክዎ የመጠየቂያ ቅፅዎን ይሙሉ፡፡ የእርስዎን የግል መረጃ ማስተካከል ካስፈለጉ ማንነትዎን ለማረጋገጥ ቀደም ሲል የተገኘውን መረጃ የመጠቀም መብታችን የተጠበቀ ነው፡፡

**አይከታተሉ**። በአሁኑ ጊዜ በድህረ-ገፅ አሳሾች ለሚላኩ "አይከታተሉ" ("DNT") ለሚሉ ምልክቶች ምላሽ አንሰጥም:: የ DNT ምልክቶች እንዴት እንደሚተረጎሙ እና በድህረ-ገፅ ጣቢያዎች እና ሶስተኛ ወገኖች ለሚቀበሏቸው ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ እንዳለበት አንድ ወጥ አቋም አልተመረጠም፡፡ ሆኖም ግን፣ በእርስዎ የአሳሽ ቅንብሮች እና የኩኪዎች ክፍል ከላይ በተጠቀሰው ግላዊነት የተላበሱ የማስታወቂያ ቁጥጥሮችን ጨምሮ መረጃዎችን መሰብሰብን እና አጠቃቀምን የመቆጣጠር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

### ማቆየት

መለያዎ በሚሰራበት ጊዜ ወይም የግል አገልግሎቶችን በሚሰጥበት ወቅት የግል መረጃዎትን እንጠቀማለን፡፡ መረጃው ከዚህ በኋላ የተሰበሰበው ለንግድ ዓላማው አስፈላጊ ሆኖ ካላስፈለገ በኋላ ግላዊ መረጃን በተገቢው ሰዓት ውስጥ እናጠፋለን፡፡ እኛ ግን ህጋዊ ግዴታችንን ለመወጣት፣ አለመግባባቶችን ለመፍታት፣ እና ስምምነቶቻችንን ለማስፈጸም የግል መረጃን እንደ አስፈላጊነቱ እንይዛለን::

## ደህንነት

ኢንተርኔት ላይ የሚተላለፉ ነገሮች 100% ደህንነት የለውም ወይም ከስህተት-ነፃ አይደሉም፡፡ ሆኖም ግን፣ መረጃዎን ከብልሽት፣ አለአግባብ መጠቀምና ያልተፈቀደ መዳረሻ፣ ይፋ ማውጣት፣ መቀየር እና ማበላሸት ለመጠበቅ ተገቢ እርምጃዎች እንወስዳለን፡፡ የእርስዎን የይለፍ ቃል እና የተጠቃሚ መታወቂያዎች ለመጠበቅ እና ለአንዱ አገልግሎታችን የተሰጠዎት የይለፍ ቃልዎ ወይም የተጠቃሚ መታወቂያዎ መጠራጠር ከጀመሩ ከታች ከተዘረዘሩት የመገናኛ መንገዶች አንዱን ለእኛ ማሳወቅ የእርስዎ ኃላፊነት ነው፡፡ በይለፍ ቃልዎ እና በይዘት መታወቂያዎ ላይ ለማንኛውም ያልተፈቀዱ የአገልግሎቶቻችን አጠቃቀም እርስዎ ብቻ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡

## የልጆች ግላዊነት

አገልግሎቶቻችን ለአዋቂዎች የታሰቡ ናቸው፡፡ በህግ በተደነገገው መሠረት ህጻናት በግል ሊለዩ የሚችሉ መረጃዎችን አንሰበስብም እናም ልጆች ማንኛውንም የግል  መረጃዎችን እንዲያቀርቡልን እንጠይቃለን፡፡

## ማሻሻያዎች

በማንኛውም ጊዜ የዚህን መመርያ የተወሰነ ክፍል የመቀየር፣ የመጨመር ወይም የማስወገድ መብት አለን፣ ነገር ግን ለውጦች በታለፈው ቀን ላይ በተሻሻለው ቀን ላይ በመምሪያው ላይ በመጠቆም ለውጡን ያሳውቆዎታል፡፡ መመሪያውን በቁሳዊ መንገድ የምንለውጥ ከሆነ፣ ቢያንስ ለሰላሳ ቀናት ያህል ተገቢ የመስመር ላይ ማስታወቂያ እንሰጥዎታለን እና/ወይም በህግ በተደነገገው መሠረት የርስዎን ግልጽ ፍቃድ እንሰጥዎታለን፡፡ ድህረ ገፃችንን ሲጎበኙ ወይም አገልግሎቶቻችንን ሲጠቀሙ፣ የዚህን መመሪያ የአሁኑ ስሪት እየተቀበሉ ነው፡፡ ማንኛውንም ለውጦች ለማወቅ ተጠቃሚዎች ይህን መመሪያ በድጋሜ እንዲመለከቱ እንመክራለን፡ ፡

## አግኙን

እኛን ለማግኘት፣ በ privacy[በ]qualcomm[ነጥብ]com ኢሜል ይላኩ፣ ወይንም በ Qualcomm Incorporated, Attn ይጻፉልን፡፡ Privacy Counsel, 5775 Morehouse Drive, San Diego, CA 92121.

**ተግባራዊ የሆነ ቀን:-** ኤፕሪል 18፣ 2018

©2018 Qualcomm Technologies, Inc. እና/ወይም ተያያዥ ኩባንያዎቻቸው፡፡